የሰ/መ/ቁ 37866

ግንቦት 19 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሙሉጌታ አባይ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን - ኑሪዬ አብተው /ነገረ ፈጅ/ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ለጉባኤው በይግባኝ የቀረበው አመልካች ሲሆን፣ ቅሬታውም በተጠሪ የተጣለብኝ መቀጫ ያለአግባብ ስለሆነ ይነሳልኝ የሚል ነው፡፡ ጉባኤው ከተጠሪ የቀረበውን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የመቀጮውን መጠን ዝቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የጉባኤውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በዚህ ደረጃም የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መቀጮን በተመለከተ በሚቀርበው ክርክር /ይግባኝ/ ላይ ስልጣን የለውም የሚል ምክንያት በመስጠት የጉባኤውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት አመልካች ያቀረበለትን ይግባኝ ውድቅ አድርጎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረቡለትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ ላይ በሚነሳው ክርክር ላይ ስልጣን የለውም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዋናው ግብር ላይ የሚጣለውን መቀጫ በመቃወም በሚቀርበው ይግባኝ ላይ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ በሰበር መ.ቁ 34691 በቀረበው ክርክር በአሁኑ በተያዘው መዝገብ የተነሣው ጭብጥ አከራካሪ ስለነበር የሰበር ችሎቱ ለሕጉ ትርጉም በመስጠት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በዚህ አይነት የሰበር ችሎቱ የሚሰጠው ውሳኔ (የሕግ ትርጉም) በችሎቱ እስካልተለወጠ ድረስ አስገዳጅ እንደሚሆን የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ 454/97 በአንቀጽ 2(4) ተደንግጎአል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 46438 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 34888 የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመቀጮ እና ወለድ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ የማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ